# ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሰጠን ተስፋና ጥርስ አልባው አንቀጽ 39

**ጌታቸው ኃይሌ**

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከታየ ጀምሮ ሰፊ ትችት ስለተካሄደ ፥ ያልተባለ ፥ ለኔ የተረፈ ነገር የለም ። "ለመሆኑ ከየትኛው የሐሳብ ወገን ነህ?" እንደተባልኩ ተረድቼ ፥ ውገናየን ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ልመልስ እሞክራለሁ ። ቀጥሎ ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ ያወዛገበን የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 አቅም ኖሮት ሳይሆን በጥላው ብቻ እንደሆነም አሳያለሁ ። ጥላ ስለማልፈራ ፥ አንቀጽ 39ን መፍራት አቁሜያለሁ ። ለዚች አጭር ድርሰት መነሻ የሆኑኝ አቶ ካሣሁን ነገዎ በአውስትራሊያ የአማርኛ ራዲዎ ጣቢያ በቅርብ ቀን የጠየቀኝ ጥያቄዎች ናቸው ።

**እንደ መቅድም ፤**

የኢትዮጵያ ሀገርነትና መንግሥት የቤተ ሰቦች ስጦታዎች ናቸው ። የአክሱም ፥ የዛጔ ፥ የአምሐራ ፥ የጐንደር ፥ የሸዋ ። ዘመነ መሳፍንትም ቢሆን የቤተ ሰብ አስተዳደር ነበር ። ሕዝብ ሲነቃ ፥ **ዘመነ ሕዝብን** ወይም **ዘመነ ዲሞክራሲን** ተመኘ ። ምኞቱ ካንዴም ሁለቴ አላዋቂዎች እጅ ገባ ፤ መጀመሪያ ደርግ ላይ ፥ በኋላ ደግሞ ኢሕአዴግ ላይ ። ምኞቱ ቀጥሏል ።

**የኢሕአዴግ የሙከራ ዘመን ። ወይም ቀዳማዊ ኢሕአዴግ**

የነፈሰውን የዐውሎ ነፋስ ለውጥ ሳይቆረቁረን ለመቀበል እንዲመቸን ፥ ኢሕአዴግ የዛሬ ሃያ ሰባት ዓመት ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ እስከዛሬ ያለውን አገዛዝ **የኢሕአደግ የሙከራ ዘመን** ወይም **የቀዳማዊ ኢሕአዴግ ዘመን** እንድንለው የዶክተር ዐቢይ አሕመድ ንግግሮች ይጋብዙናል ። በዚህ ዘመን ብዙ ስሕተቶች ተሠርተዋል ። ስሕተቶቹን የማያውቅ ስለሌለ ከዝርዝሩ አልገባም ። የኢጣልያን የፋሺስት ዘመን የሚያስመሰግን ነበር ብሎ ማለፉ ይሻላል ። ዘመኑን የሙከራ ዘመን ብለን ከወሰድነው ፥ በሙከራው (በመከራው) ዘመን የተደረገን ስሕተት እንዳይደገም ማድረግ እንጂ ወደኋላ ተመልሶ ማረም ወይም ጥፋተኛውን መቅጣት ተገቢ አይሆንም ። የዶክተር ዐቢይ አሕመድ አቋም "በዚህ እንለፈው" የሚል ነው ።

**ዳግማዊ ኢሕአዴግ ።**

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በጠቅላይ ሚኒስተርነት በነገሠ ጊዜ የተጀመረውን የኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን **ዘመነ ዳግማዊ ኢሕአዴግ** ልንለው እንችላለን ። በዚህ ዘመን በቀዳማዊ ኢሕአዴግ ዘመን የተደረጉ ስሕተቶች ይታረማሉ ፤ የፖለቲካ እስረኞች ይፈታሉ ። ከሕዝቡ ጋር አብሮ የተጨቆነው ኢትዮጵያዊነት ተፈቶ ያለመልማል ። የሚያኮራን ታሪካችን እንደዱሮው እንዲያኮራን እሱም ከእስረኞቹ ጋር አብሮ ይፈታል ። የወያኔ ትግሬዎች የፈለጉትን የሚገድሉበት ዕድል ይሰረዛል ። የኅሳ መለዮ ካርድ ይቃጠላል ። ሕገ መንግሥቱ ይከበራል ።

ይህ ሕልሜ ነው ወይስ እውነት? ብዙዎቹ ጉዳዮች በአለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ተፈጽመዋል ። ይህን ካላደረገ ብለን ሳንጨርስ የምንመኘውን ያደርጋል ። ከዚህ የበለጠ ፍጠን ማለት ፥ ሲሮጥ ተሰናክቶ ባፍ ጢሙ እንዲደፋ ማድረግ ይሆናል ። በቀዳማዊ ኢሕአዴግና በዳግማዊ ኢሕአዴግ መካከል ያለው ትልቅ ወንዝ በተራቡ አዞዎች የተሞላ ነው ። ዶክተር ዐቢይ ተጠንቅቆ እያደባ ፥ ምናልባትም ለአዞዎቹ ምናምን እየጣለላቸው ካልዋኘ ፥ ሊበሉት ይችላሉ ። "በሰላም እንዲሻገር ሕዝብ ይደግፈው ፤ አበጀህ እያልን እንጨቁህ" የምንለው ፥ አዞዎች ጩኸት እንደሚፈሩ ስለምናውቅ ነው ። ድፍረቱንና ጀግንነቱን ማድነቅ ግዴታችን ነው ።

### የዶክተር ዐቢይ አሕመድ እርምጃ

የዶክተር ዐቢይ አሕመድ አመጣጥ እግዚአብሔር "የሕዝቤን ዋይታ ሰምቻለሁ" ብሎ ሙሴን ያስነሣውን ይመስላል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዱሮም ራብተኛ ነበር ። በዘመነ ኢሕአዴግ ግን የደረሰበት ረኀብ አምሳያ የለውም ። ሕዝቡ ምናምን ቀምሶ ለማደር የሚያደርገውን ለመስማት ይከብዳል ። ለምሳሌ ፥ ደርግ ቤታቸውን ለወሰደባቸው ሰዎች በወር 250 ብር መድቦላቸው ነበር ። ዛሬም ፥ ከሠላሳ አምስ ዓመት በኋላ ፥ የሚከፈላቸው ያንኑ በአሁኑ ገበያ አንድ ቁና ጤፍ የማይገዛ 250 ብር ነው ። ቢያንስ ቢያንስ 2300 ብር መሆን ነበረበት ።

ዶክተር ዐቢይ አሕመድን የኢትዮጵያ አምላክ የላከው ለመሆኑ አራት ነገሮች አሳምነውኛል ፤ አንደኛ ፥ በደስታ እንድንኖር ተስፋ የሰጠን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ነው ። ሁለተኛ ፥ በሞት የተፈረደባቸውን እስረኞች ሳይቀር አስፈታ ፤ ሦስተኛ ፥ በሚሠራው ሥራ የሚጠሉት ሰዎች የሚጽፉበትን አያለሁ ። አራተኛ ፥ ከአቶ ይልማ መገርሳ ጋር ያለው መልካም ግንኙነት ነው ። የእግር ኳስ ጨዋታ ስለምወድ ፥ ይኸንን ከዚያ ምሳሌ በማምጣት ላስረዳ ፤ አንድ ቡድን የሚያሸንፈው ብዙ አይቶ (ግብ) ሲያስቆጥር ነው ። አስቆጣሪውን ተጫዋች ጓደኞቹ ያቅፉታል ፥ ክብር ይሰጡታል ። ጥሩ ተጫዋች እሱ ቢያገባ ክብር እንደሚያገኝ እያወቀ ፥ የራሱን ዕድል ከተጠራጠረ ፥ ኳሷን ለሌላው ተጫዋች ያቀብላታል ። አቶ ለማ መገርሳ ለሥልጣን ሳይጓጓ ለኢትዮጵያ ስላሰበ ፥ ዶክተር ዐቢይ አሕመድን አስቀደመ ።

ዶክተር ዐቢይ በመነሣቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእግዚአብሔር ምስጋና እያቀረበ ነው ። የበለጠ ድጋፍ የሚያገኘው ፥ ማንም ኢትዮጵያዊ በመረጠው ቦታ የመኖር መብት አለው የሚለውን የሕገ መንግሥት አንቀጽ ሲያስከብር ነው ። በአሁኑ ሰዓት ይህ አንቀጽ የሚጣሰው ከባለ ሥልጣን በጽሑፍ በተሰጠ ትእዛዝ መሆኑን ዶክተር ዐቢይ ያውቃል ። በደል የሚደርሰው በኦሮሞዎች ላይ ጭምር ነው ። ይኸንን እንዲያስቆም እያሳሰብን ፥ ለማቆም የተቸገረበት ነገር ቢኖር ነው ብሎ ማሰብም ተገቢ ነው ።

የዶክተር ዐቢይ አሕመድ እርምጃ የቅኔ መምህራን ኀብር የሚሉት ዓይነት ነው ። ለኀብር ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ምሳሌ አልቃሿ ፥ "ዓምና ነበር እንጂ ዘንድሮስ የለህም" ያለችው ነው ። የሚናገረውና የሚሠራው አብዛኛውን ጊዜ ፥ ማንኛውም ቡድን "ዐቢይ ወገኔ ነው" እንዲል አድርገውታል ። አንድነቶች

ሚዛኑ ወደነሱ እንዲያጋድል ከፈለጉ ፥ “ከናዝሬት ደግ ሰው አይወጣም” ማለታችንን ማቆም ፥ በርታ ማለት ፥ ዘዴ መስጠት አለባቸው ።

ሆኖም ፥ ወያኔዎች የራሳቸውን ሕገ መንግሥት ከተቃወሙ ፥ የሁለት ኀይሎች ፍጥጫ ይፈጠራል ። ሁለቱ ኃይሎች የምላቸው በአንድ ወገን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ በሌላ ወገን ወያኔዎች ራሳቸው እየደለቡ በፍርፋሪ የቀጠሩት የጦር ኃይላቸው ናቸው ። በዚህ ፍጥጫ ጊዜ ወያኔዎች በዘረፉት ገንዘብ ለመጠቀም ሲሉ የሚያፈገፍጉ ይመስለኛል ። ዱሮውንም አነሣሣቸው የተሳሳተ ነበር ። የትግራይን ሕዝብ ድጋፍ ያገኙት የትግራይን የበላይነት ፥ የትግሬዎችን ገዢነት ለማረጋገጥ ነው እያሉ ነበር ። እውነትም ለጊዜው ጌቶች አድርገዋቸዋል ። ማንኛውም ትግሬ ከአቶ አሰፋ ማሩ ጀምሮ የፈለገውን ትግሬ ያልሆነ ኢትዮጵያዊ መግደል ይችል ነበር ። ግን ለትግራይ ልጆች ለወዲያኛው ያተረፉላቸው ነገር ቢኖር ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ መጠላትን ነው ። ኢትዮጵያ ላይ የፋሽስት ጣልያኖች የዛሬዎቹን ትግራዮች ያህል አልተጠሉም ። አንዲት የትግራይ ሴት “በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ሹሩባችንን እያሳየን መራመድ አልቻልንም” እያለች ዋይታዋን ስታሰማ ሰምቻለሁ ። በምን ምክንያት እንደሆነ ግን አላወቀችውም ።

**ባዶ አንቀጽ** 39

ኢሕአዴጎችን ያልተቀበልናቸው ፥ በሁለት ምክንያት ነው ፤ አንደኛ ፥ በሕገ መንግሥታቸው ስለከፋፈሉን ፤ ሁለተኛ ፥ በሕገ መንግሥታቸው በወረቀት ያጸደቁልንን መብት በሥራ ስለነፈጉን ነው ። ሕገ መንግሥታቸው ውስጥ የምንወዳቸውና የምንጠላቸው አንቀጾች አሉ ። ዶክተር ዐቢይ የምንወዳቸውን አንቀጾች ካስከበረልን ትልቅ ውለታ ነው ። ምናልባትም ከዚያ የበለጠ ምኞት ላይኖረን ይችላል ። የአንድነት ወገኖች የማንወደው ሕግ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 39 ነው ።

ዶክተር ዐቢይን ማድረግ የማይችለውን ፥ “እኛ የማንወደወዳቸውን አንቀጾች ከሕገ መንግሥቱ ሰርዝልን” ከማለት ፥ ማድረግ የሚችለውን “ሕገ መንግሥቱን አስከብር” ብንል ይሻላል ። ግን ሕገ መንግሥቱ ከተከበረ ፥ በተለየ አንቀጽ 39 በራሱ ተገርስሶ ይወድቃል ። ምክንያቱም አንቀጽ 39ን ጠጋ ብሎ ላየው ድቡሽት ላይ የተሠራ ባዶ ቤት ሆኖ ያገኘዋል ። ምን ማለቴ እንደሆነ ላስረዳ ።

ሕገ መንግሥቱ አንደኛ ፥ እመግቢያው ላይ ኢትዮጵያ የብሔሮች ፣ ብሔረሰቦች ፣ ሕዝቦች አገር መሆኗን በይፋ ያውቃል ፤ በእንግሊዝኛው nations, nationalities, and peoples ይላቸዋል ። ነሳዎቹንና ነገዶቹን ነው ። ሁለተኛ ፥ አገሪቱን በአንቀጽ 47 ከዘጠኝ የፌዴራል ክልል (States) ይከፍላታል ። አንቀጽ 39 የመገንጠል መብት የሚሰጠው ለእነዚህ በክልሎቹ ውስጥ ለሰፈሩት ነሳዎችና ነገዶች እንጂ ፥ በጠቅላላው ለክልሎቹ አይደለም ። ሕገ መንግሥቱን ልጥቀስ ፤

> “1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ፣ ብሔረሰብ ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው ። 4. የብሔር ፣

ብሔረሰቦች ፥ ሕዝቦች የራሱን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት ከሥራ ላይ የሚውለው (ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው ።)

ሀ) የመገንጠል ጥያቄ በብሔር ፥ በብሔረ ሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ ፥"

አንደኛ ፥ እነዚህ ጎሳዎች ስንት እንደሆኑ አይታወቅም ። ጎሳዎች የሌሉበት ክልል ስለሌለ ፥ በየክልሉ ተፈልገው ቢቆጠሩ ወደ ሰማንያ ይደርሳሉ ይባላል ። ሁለተኛ ፥ ከሰማንያዎቹ ጎሳዎችና ነገዶች አንዳቸውም በሁለት ሦስተኛ ውሳኔ የሚያሳልፍ "የሕግ አውጪ ምክር ቤት" ያለው የለም ።

በመጨረሻ ፥ አንቀጽ 41.1. እንዲህ ይላል ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው ። (እንግሊዝኛው የበለጠ ግልጽ ነው ፤ "Every Ethiopian citizen has the right to engage freely in economic activity and to pursue a livelihood anywhere in the national territory.")

በሕገ መንግሥቱና በሕዝብ መካከል አለ መግባባት የተፈጠረው የስያሜ ቃላት ባለመስተካከላቸው ነው ። ዋናው መደንቀፍ "ክልል" የሚለው ስያሜ ነው ። "ክልል" ሲባል አንድ ክልል አጥር ሆኖ በውስጡ የሚኖሩ ዜጋዎች የግል ንብረት ያስመስላል ። ልክ ማዘጋጃ ቤት የከተማ ቦታ ዳር ድምበር ከልሎ ፥ ካርታ አውጥቶ ለአንድ ሰው እንደሚያስከብር ። ሐሳቡ ይኼ እንዳልሆነ ሁለት ነጥቦች ይመሰክራሉ ፤ አንደኛ ፥ እንግሊዝኛው "States" ማለቱ ፣ ሁለተኛ ፥ በያንዳንዱ ክልል ውስጥ "ብሔሮች ፥ ብሔረሰቦች ፥ ሕዝቦች" መኖራቸውን ማወቁ ። ስማቸውን መልአክ ሳወጣው ቀርቶ ነው እንጂ ፥ ክልሎች ብሔራዊ የአስተዳደር ክፍሎች ፥ ራስ-ገዝ ግዛቶች ናቸው ። ሁኔታው ይህ ከሆነ ፥ ጥያቄያችንን እናስተካልክ ፤ "ወደጥንቱ ወደታሪካዊው አከፋፈል እንመለስ ። ይኸም ካልሆነ ፥ "አንድ ክልል ከፈለገ ሊገነጠል ይችላል" የማይለው ሕገ መንግሥት ይከበር ።

አንድ አውቶቡስ ብዙ ሰዎች ተሳፍረዋት ከአዲስ አበባ ወደደቡብ ስትበር ትታየኛለች ። መንገደኞቹ የተሳፈሯት ወደሚፈልጉት ከተማ እንደምትወስዳቸው በመተማመን ነው ። ግን የሁሉም መድረሻ አንድ መሰላቸው እንጂ አንድ አይደለም ። የሻሸመኔና የናዝሬት መንገደኞች ናቸው ። ቁርጡን የሚያውቁት ሞጆ ላይ ሲደርሱ ነው ። አውቶቡሷ እዚያ ስትደርስ ነጂው ሁሉንም መንገደኞች ይዞ ወይ ወደናዝሬት ወይም ወደዝዋይ የሚወስደውን መንገድ ይዞ ይበራል ።